የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority

10/749

17 መጋቢት 2006

**በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ**
**<u>በያሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፣</u>**

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና አሠራር መመሪያ ቁጥር 91/2006ን ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 95/2006 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከላችሁ መሆኑን እያስታወቅኩ፣ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

በከር ሻሌ ዱሌ
ዋና ዳይሬክተር

**<u>ግልባጭ፣</u>**

- ለኦፕሬሽን ፕሮግራም ዲዛይንና ልማት ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር
- ለለውጥና ሞደርናይዜሽን ሥራዎች ዘርፍ ም/ዋ/ዳይሬክተር

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

16/7/06

## የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 91/2006ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር ..................

በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2006 መሠረት ለሚቀርቡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት የቅሬታ ኮሚቴዎች ስልጣን የግብር ከፋዮችን ደረጃና አከራካሪ የሆነውን የግብር/ታክስ መጠን መሰረት በማድረግ እንደገና መወሰንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ይበልጥ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በግብር/በታክስ ህጎች እና በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 587/2000 በአንቀጽ 8(3) እና አንቀጽ 20(2) መሠረት ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 91/2006 ለማሻሻል ይህን መመሪያ ቁጥር 95/2006 አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 91/2006ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 95/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

   የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቋቋሚያና የአሰራር መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

   1. የመመሪያው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 ተሰርዞ እንደ ቅደም ተከተላቸው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 ተተክቷል።

      1. ከፍተኛ ግብር ከፋይ የሆነ የተወሰነበትንና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 20,000,000 (ሃያ ሚሊየን) በላይ ከሆነ፣ ወይም
      2. መካከለኛ ግብር ከፋይ የሆነ የተወሰነበትንና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 5,000,000 (አምስት ሚሊየን) በላይ፣ ወይም
      3. አነስተኛ ግብር ከፋይ ከሆነ የተወሰነበትንና ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የግብር እና ታክስ መጠን ወለድና መቀጫን ጨምሮ ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊየን) በላይ የሆኑትን ጉዳዮች ብቻ ነው።

2. በመመሪያው አንቀጽ 11 "በቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚቋቋም ኮሚቴ ስልጣን" በሚለው ስር ሁለት ንዑስ አንቀጾች እንዲኖሩ ተደርጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1. በመመሪያው አንቀጽ 10 መሰረት በዋና መስሪያ ቤት ከሚታዩት ጉዳዮች ውጪ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
   2. ለአቤቱታ መነሻ የሆነው ወይም አከራካሪ የሆነው የግብር እና የታክስ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ ማናቸውም የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የማይገደዱ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ወይም የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚገደዱ የደረጃ "ሀ" ወይም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች ሆነው ነገር ግን የሂሳብ መዝገብ ባለመያዛቸው የዕለት ገቢ ግምትን መሠረት በማድረግ ግብር/ታክስ የተወሰነባቸው ግብር ከፋዮች የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

3. በመመሪያው ከአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 በኋላ ቀጥሎ የተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተጨምሯል፡፡

   3. ይህ የመመሪያው ማሻሻያ ፀድቆ ከመውጣቱ በፊት የቀረቡ አቤቱታዎች በቀረቡለት ኮሚቴ ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡

4. <u>መመሪያው የሚፀናበት ቀን</u>

   ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት ..... ቀን 2006 ዓ.ም.

በከር ሻሌ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር